እያለ ልጅቱ የተወለደተች መሆኑን በማስረጃ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው እነዚህን ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ያስረዱልኛል ብሎ የቆጠራቸውን ምስክሮች አልሰማም፡፡ ተጠሪው የልጅቱ አባት መሆኑን በማስረጃ ካላስረዳ የልጅቱ አክስት የሆኑ ተጠሪዎች ማንም አባት ነኝ ብሎ ለመጣ ሰው ልጅቱን አሳልፈው እንዲሰጡ የሚያስገድዳቸው የሕግ ድንግጌ የለም፡፡ የልጅቱ አባት ያልሆነ ሰው አባቷ ነኝ ብሎ ሲቀርብም የልጅቱ አባት አይደለም፣ ስለዚህ በአግባቡ አያሳድጋትም የሚለውን ምክንያት አንስተው እንዳይከራከሩ የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 147 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 አይገድባቸውም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማ ተጠሪው የሕፃኗ አባት ስለሆነ አስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔና የጠቅላይ ፍርድ  ፣ኔው የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በ‹ በው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 5947 ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ አመልካች ለራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34387

ነቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
መድሕን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ከበደ ሙሔ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51375 ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 32029 ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ

በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው። የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በሕጋዊ ጋብቻ ተሣሥረው ለበርካታ ዓመታት በባልና ሚስትነት የኖሩ ሲሆን፣ ጋብቻቸውን በፍች አፍርሰዋል። ከዚህ በኋላ የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጋራ ንብረት ዝርዝር አቅርበው ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል። አከራካሪው ጉዳይ ተጠሪ እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የተቀበሉት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲከፈለኝ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው ነው። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የጡረታ አበል ይሰጠኝ ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል። ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት በከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፣ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል የጋራ ንብረት ነው በማለት የጡረታና ማኀበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ከግንቦት ወር 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን የሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል። አመልካች አሁን የማገኘው አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ብር የጡረታ ገንዘብ ወታደር ቤት እያለሁ በአይኔ ላይ ጉዳት ደርሶብኝ በቦርድ በመውጣቴ የማገኘው ነው። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ተጠሪዋ ግማሹን እንድትወስድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩሏ የጡረታ አበሉ በትዳራችን ጊዜ የተጠራቀመ በመሆኑ ግማሹን እንድወስድ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለች ተከራክራለች።

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ግራ ቀኙ የሚያነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዋ ከግንቦት 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ልታገኝ ይገባታል በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ አይተናል።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔውን በሚሰጥበት ወቅት የተከተለውን ሥርዓት ስንመረምረው፣ ተጠሪ የጡረታ አበል፣ ታስቦ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የወሰዱትን የጡረታ አበል መሆኑን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣነው በግልጽ አስፍሮታል። ይህ ከሆነ ተጠሪ የጠየቁትን ጋብቻቸው ከመፍረሱ በፊት ተለያይተው እያለ አመልካች ተቀብለው የተጠቀሙበት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲሰጣቸው እንጂ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ አመልካች ከሚያገኙት የጡረታ አበል ግማሹን እንዲወስንላቸው በሥር ፍርድ ቤት አልጠየቁም። ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላቀረቡትንና በሥር ያልተከራከሩበትን አዲስ ነገር በይግባኝ ደረጃ ለማንሣትና ለመጠየቅ እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥ ... ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል። ስለሆነም ተጠሪ በሥ ... ቁትና ያልተከራከሩትን ጉዳይ በማንሣት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከግንቦት ወር 1999 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካች ከሚያገኙት ጡረታ ግማሹን ሊከፍላት ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል፣ የመንግሥት ሠራተኛ በነበሩበት ሠዓት ከደመወዛቸው ተቆርጦ የተጠራቀመ ነው የሚለው አባባል መሠረታዊ ስህተት ያለበትና የጡረታ አበሉ መንግሥት በኩል ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ያለ በመሆኑ ለአንድ ሠራተኛም የጡረታ አበል የሚከፈለው እድሜው በገፋበትና ጉልበቱ በደከመበት ጊዜ መጦሪያ የሚሆነውና ለመኖር የሚያስፈልገውን ወጭ በከፊልም ቢሆን በመሸፈንና ለማኀበራዊ ደህንነቱ ዋስትና ለመስጠት መንግሥት ካለው የማኀበራዊ ደህንነትና ዋስትና ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ እንደማንኛውም ገቢ የጋራ ንብረት ነው የሚባል አይደለም። የአንድ ሰው የጡረታ አበል በማናቸውም መልኩ በዕዳ ሊያዝ ወይም ሊታገድና ሊቀነስ እንደማይችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ